# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት
# ልሣነ- ሕግ ጋዜጣ

17ኛ ዓመትአዋጅ
ቁጥር 101 ነሐሴ
2003 አሶሳ

## ማውጫ

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት የአስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት ፣ ስልጣንና ተግባራቸውን እንደገና ለመወሰን የወጣ አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር101/2003

የክልሉን አስፈጻሚ የመንግሥት አካላት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 94/2ሺ3ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአስፈጻሚ የመንግሥት አካላትን አደረጃጀትና አወቃቀር ስያሜ ከታችኛዎች እርከን በመ/ቤቶች ጋር ለመለየት የማያስችል በመሆኑና ይህንን ማስተካከል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት አባል የሆኑ አስፈጻሚ የመንግሥት አካላት አደረጃጀት ወጥነት እንዲኖረው ማድረጉ ካላቸው የሥራ ስፋትና የሰው ሃይል አንፃር ተገቢነት ያለው በመሆኑ፣

የክልሉ ም/ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 49/3:1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### አንቀጽ 1 ስያሜ እና ማቋቋም

1. የክልሉን አስፈጻሚ አካላት አንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 94/2003 አንቀጽ 9/11/ የተቋቋሙት ክልሉ የመንግሥት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት በአዋጁ

   የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ካለው ሰፊ የሰው ሃይልና የሥራ ስፋት አንጻር የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመንግሥት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ በሚል በዚህ አዋጅ ስያሜው ተስተካክሏል፡፡

2. የክልሉን አስፈጻሚ አካላት እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 94/2003 አንቀጽ 9/5/ የተቋቋመው የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤትም በዚህ አዋጅ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በሚል ተቀይሯል፡፡

### አንቀጽ 2 አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልል ም/ክር ቤት ፀድቆ በልሳነ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አህመድ ናስር አህመድ
የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት
ፕሬዚዳንት

ነሐሴ 2003

<u>አሶሳ</u>